מדינת ישראל
משרד האוצר

רשות המסים בישראל

# የገቢ ስጦታ

## ከዛሬ ጀምሮ መሥራት ያዋጣል



ለ2015 የቀረጥ ዓመት፣ ለደመወዝተኞችና በግል ለሚሠሩ

## የሥራ ስጦታ ("ማዓናክ ዓቮዳ) ፕሮግራም

ከሥራ ስጦታ (ቀድሞ "ማስ ሃክናሳ ሽሊሊ" ይባል የነበረው) ፕሮግራም ዓላማዎች አንዳንዶቹ ሰዎች በሥራው ዓለም እንዲሳተፉ ማነቃቃት፣ ዝቅተኛ ደመወዝ የሚቀበሉ ሠራተኞች ገቢን ማሳደግና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶችን ማጥበብ ነው።

## ለ2015 የቀረጥ ዓመት የስጦታው ባለመብት ማን ነው?

ሕጉ ተፈጻሚ የሚሆነው በ2015 የቀረጥ ዓመት ላይ ከሥራ ገቢ፣ ከንግድ ገቢ ወይም የእጅ ሙያ ገቢ በነበረው ማንኛውም ተቀጣሪ ወይም ለግሉ ከሚሠራ ሠራተኛ ላይ ሲሆን የሚከተሉትን ሦስት መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

1. ዕድሜህ 23 ዓመት የሆነና ልጆች ያሉህ ከሆነ ወይም ዕድሜህ 55 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆንክና ልጆች የሌሉህም ከሆነ።
2. በ2015 ዓ.ም. ከአንድ መኖሪያ ቤት ውጪ በአንተ፣ በሚስትህና በአንተ ዘንድ ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት ባላቸው ልጆች እጅ ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት (**"ዘሁት መካርከዒን"**) ለምሳሌ አፓርተማ፣ ሱቅ፣ መሬትና የመሳሰሉት) **ከሌለ።** ይህም በእስራኤል ወይም ከእስራኤል ውጪ የሚገኘውን ንብረት የሚጨምር ሲሆን ባለቤትነቱ ከ50% በላይ ከሆነ ነው።
3. በአንተ ላይ ከእነዚህ ከሁለቱ ነገሮች አንዱ ተፈጻሚ ከሆነ፡
   - 3.1 **አንድ ወይም ሁለት ልጆች ያሉህ ከሆነ ወይም ዕድሜህ 55 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆንክና ልጆች የሌሉህም ከሆነ -**
     የሚገኘው ውጤት ማለትም ከማንኛውም ሥራ/ንግድ/ከእጅ ሙያ የሚገኝ ገቢ በ2015 የቀረጥ ዓመት **ለሠራህባቸው** ወራት ይከፈላል (ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም ለግልህ የምትሠራ ሠራተኛ ከሆንክ ነገር ግን ከ12 ወራት የማይበልጥ)። በዚህ ዓመት **ከ2,060 ሼቄል የሚበልጥና ከ6,141 ሼቄል የሚያንስ ነው።***
   - 3.2 **ሦስት ወይም ከዚያ የበለጡ ልጆች ያሉህ ከሆነ** - የሚገኘው ውጤት ማለትም ከማንኛውም ሥራ/ንግድ/የእጅ ሙያ የሚገኝ ገቢ በ2015 የቀረጥ ዓመት **ለሠራህባቸው** ወራት ይከፈላል (ተቀጣሪ ሠራተኛ ወይም ለግልህ የምትሠራ ሠራተኛ ከሆንክ ነገር ግን ከ12 ወራት የማይበልጥ)። በዚህ ዓመት **ከ2,060 ሼቄል የሚበልጥና ከ6,750 ሼቄል የሚያንስ ነው።***

* የገንዘቡ መጠን በ1.6.2015 የወጣውን "ማዳድ" የሚያንጸባርቅ ሲሆን በሕጉ መመሪያ መሠረት በ1.6.2016 ይሻሻላል።

## ለአካለ ስንኩል ሠራተኞች የሚሰጥ ስጦታ

ሕጉ **"የተስተካከለ ዝቅተኛ ደመወዝ"** የሚያገኙ አካለ ስንኩል ሠራተኞችን የሚረዳ ነው። በመሆኑም አካለ ስንኩል ሠራተኞች መብት የሚያስገኝላቸው ገቢ አካለ ስንኩል ካልሆነው ሠራተኛ ገቢ ያነሰ ቢሆንም ለስጦታው ባለመብት ይሆናሉ።

**ማብራሪያዎች፡**

**ተቀጣሪ ሠራተኛ** - የእስራኤል ኗሪ የሆነ ግለሰብ በ2015 የቀረጥ ዓመት የሥራ ገቢ የነበረው። ተቀጣሪ ሠራተኛው ላይ ከሚከተሉት መስፈርቶች ውስጥ አንዱ እንኳን ተግባራዊ ከሆነ ሕጉ ተፈጻሚነት የለውም።

ሠራተኛው የሥራ ገቢውን በሙሉ የተቀበለው "ቅርብ" ወይም "ጓደኛ" ከሆነ አሠሪ ከሆነና እሱ ወይም "የቅርቡ" በኩባንያው ላይ ቁጥጥር ካላቸው (ማለትም በኩባንያው ያላቸው ድርሻ 10% እና ከዚያ በላይ ከሆነ)።

እንደዚሁም ሠራተኛው በሥራው ወራት የሥራ ገቢውን የ"ቅርብ" ካልሆነ አሠሪ እንደዚሁም በተጨማሪ የ"ቅርብ" **ከሆነ** አሠሪ ተቀብሎ ከሆነ ነው።

እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ሠራተኛው ገቢውን የ"ቅርብ" **ካልሆነ** አሠሪ እንደዚሁም የ"ቅርብ" **ከሆነ** አሠሪ ተቀብሎ ከሆነ የስጦታ ባለመብት የሚሆነው የ"ቅርብ" ከሆነ አሠሪ ገቢ **ላልተቀበለባቸው** ወራት **ብቻ** ነው። በዚህ አንቀጽ ሥር **"ቅርብ"** የሚባለው፡ የትዳር ጓደኛ፣ ወንድም፣ እኅት፣ ወላጅ፣ የወላጅ ወላጆች፣ ልጅ፣ የባልና ሚስቱ ልጆች እንደዚሁም የእነዚህ ሁሉ የትዳር ጓደኛ ነው።

**ምሳሌዎች፡**

1. ማመልከቻውን ያቀረበው ከጥር እስከ ታኅሣሥ ድረስ "የቅርብ" **ከሆነ** አሠሪ የሥራ ገቢ ከነበረው እንደዚሁም ከጥር እስከ ሐምሌ ድረስ "የቅርብ" **ካልሆነ** አሠሪ የሥራ ገቢ ከነበረው ስጦታውን ለመቀበል **መብት የለውም።**
2. ማመልከቻውን ያቀረበው ከጥር እስከ ሐምሌ ድረስ "የቅርብ" **ከሆነ** አሠሪ የሥራ ገቢ ከነበረው እንደዚሁም ከጥር እስከ ታኅሣሥ ድረስ "የቅርብ" **ካልሆነ** አሠሪ የሥራ ገቢ ከነበረው ስጦታውን ለመቀበል **መብት ያለው** ከነሐሴ እስከ ታኅሣሥ ላሉት ወራት **ብቻ** ነው።

***"የሥራ ገቢ"*** - ደመወዝ (ከጡረታ ውጪ) ከቤት ውስጥ ሥራዎች የሚገኝ ገቢ፣
ከአሠሪው ለሠራተኛው የተሰጡ ጥቅማጥቅሞች (ሠራተኛው ወጪውን እንዲሸፍንበት የተሰጠው ክፍያ፣ መኪና እና ስልክ ይጨምራል፣ የትምህርት ክፍያ፣ የውጭ አገር ጉዞ፣ የሙያዊ መጻሕፍት ግዥ፣ አልባሳት፣ ወዘተ.)፣ የወሊድ ክፍያ፣ የእርግዝና መጠበቂያ ክፍያ፣ በቢቱዋሕ ሌኡሚ መሠረት የሚከፈል የተጠባባቂ ውትድርና ("ሚሉኢም") ክፍያ።

***"ተጨባጭ (እውነተኛ) የሥራ ወራት"*** - ዓመታዊ ዕረፍት ፣ የታመምክባቸው ጊዜያት፣ የወሊድ ዕረፍት ጊዜና የእርግዝና መጠበቂያ ጊዜ በቢቱዋሕ ሌኡሚ ሕግ መሠረት። በቢቱዋሕ ሌኡሚ ሕግ መሠረት የሥራ አጥነት ክፍያ ከተከፈለባቸው ወራት ውጪ ያለ የተጠባባቂ ውትድርና ("ሚሉኢም") አገልግሎት።

***"ለግሉ የሚሠራ ሠራተኛ"*** - በ2015 የቀረጥ ዓመት ከንግድ ወይም ከሥራ ገቢ የነበረው የእስራኤል ኗሪ የሆነ ግለሰብ።

***"ልጅ"*** - በ2015 የቀረጥዓመት ገና 19 ዓመት ያልሞላው።

ለምሳሌ፡ ስጦታን ለመቀበል በ2016 ዓ.ም. ለቀረበ ማመልከቻ (ለ2015 የቀረጥ ዓመት) እስከ 31.12.15 ድረስ ልጁ የ19 ዓመት ዕድሜ መሆን የለበትም።

## ስጦታውን ለመቀበል መስፈርቶቹ ምንድን ናቸው?

1. ስጦታውን ለመቀበል ማመልከቻ ማቅረብ ያስፈልጋል (ቀጥሎ እንደተዘረዘረው)። ለ2105 ዓ.ም. የቀረጥ ዓመት ስጦታ ለመቀበል ማመልከቻውን እስከ **መስከረም 30 ቀን 2016** ድረስ ማቅረብ ያስፈልጋል።
2. ለ"ማስ ሀክናሳ" ሪፖርት ማቅረብ ያለበት "ለግሉ የሚሠራ"/"ሠራተኛ" (ተቀጣሪ) ወይም ሪፖርት ማቅረብ ያለበት የትዳር አጋር **ዓመታዊ ሪፖርቱን** የሚያቀርበው እስከ **ሰኔ 30 ቀን 2016** ዓ.ም. ሲሆን የሚፈጸመውም በኢንቴርኔት አማካይነት ነው። ግልጽ መሆን ያለበት...የሪፖርቱ ማቅረቢያ ጊዜ የተራዘመለት ግለሰብ በዚያ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ አለበት።
3. ለታክስ ዓመት 2015 ሪፖርት 126/856 በኢንቴርኔት አማካይነት በአሠሪው አማካይነት እስከ **ሚያዚያ 30 ቀን 2016** ድርስ ቀርቦ ከሆነ።

## የይገባኛል ማመልከቻ እንዴት ነው የሚቀርበው?

**አስተውል፡** ማመልከቻው ግላዊ ስለሆነ በሌላ ሰው ስም ማመልከቻ ማቅረብ አይቻልም። የግለሰቡን መታወቂያ በመያዝ ወይም ውክልና በማቅረብ ጭምር ማመልከት አይቻልም። **ማመልከቻን ማቅረብ ምንም ዓይነት ክፍያ አይጠይቅም።**

**ስለሆነም ማመልከቻውን ለማቅረብ በክፍያ አገልግሎት መታገዝ አያስፈልግም!**

**የሥራ ስጦታን ለመቀበል ማመልከቻውን ሁለት አማራጮች ተጠቅሞ ማቅረብ ይቻላል፡ "መኩቫን" በሆነ ቅጽ አማካይነት ወይም በፖስታ ቤት ቅርንጫፎች አማካይነት። ይህም እንደሚከተለው ነው፡**

1. **"መኩቫን" በሆነ ቅጽ አማካይነት** - ይህ የሚቻለው **ካሁን በፊት** ማመልከቻውን በፖስታ ቤት ቅርንጫፍ/ በዋጋ መተመኛ ("ሹማ") መሥሪያ ቤት/ "ሜኩቫን" በሆነ መንገድ በኢንቴርኔት ላቀረበ ግለሰብ (ካለፉት ሁለት የማመልከቻዎች ዓመታት ውስጥ በአንዱ) ነው። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ WWW.TAXES.GOV.IL ወደተሰኘው የግብር አገልግሎት ባለሥልጣን ድረ-ገጽ መግባት ያስፈልጋል።
   - **1.1** የግል ዝርዝሮችን መሙላት - አንቀጽ 2.1ን ተመልከት (የባንክ ሒሳብ መረጃዎችን ከመሙላት በስተቀር)።
   - **1.2** የመለያ ጥያቄዎችን መመለስ።
   - **1.3** ሰነዱን ማረጋገጥና የሰነዱን ቅጽ ማተም።

* ግልጽ መሆን ያለበት የስጦታው ገንዘብ የሚተላለፈው በግብር አገልግሎት ባለሥልጣን ዝርዝር እጅ ወደሚገኝ የባንክ ሒሳብ ነው።

* ለ2014 እና 2015 የቀረጥ ዓመት የሥራ ስጦታ ለመቀበል በዚህ ድረ ገጽ አማካይነት ማመልከት ይቻላል።

2. **በፖስታ ቤቶ ቅርንጫፎች አማካይነት** - ማመልከቻውን ለማቅረብ በመላ እስራኤል ተሰራጭተው ከሚገኙት **ፖስታ ቤቶች** ውስጥ ወዳንዱ ራስህ መሄድ አለብህ። ስትሄድም **የመታወቂያ ወረቀት እና ቼክ** ወይም **በራስህ ስም የባንክ ሒሳብ እንዳለ የሚያረጋግጥ የባንክ ሕጋዊ ማስረጃ** ይዘህ ሂድ። የስጦታው ገንዘብ የሚተላለፈውም ወደዚሁ የባንክ ሒሳብ ነው።
   - **2.1** በፖስታ ቤቱ ለሠራተኛው ራስህን አስተዋውቅና የሚከተሉትን መረጃዎች ስጠው፡
     - **ሀ.** በ2015 የቀረጥ ዓመት ላንተና ለትዳር ጓደኛህ የነበሩ አሠሪዎች ብዛት (በቤት ውስጥ የሚያሠሩትን ጨምሮ)
     - **ለ.** በ2015 የቀረጥ ዓመት "የግል ሥራ" ከነበረህ።
     - **ሐ.** የፖስታ መላኪያ አድራሻ።
     - **መ.** የስጦታው ገንዘብ የሚገባበት የባንክ ሒሳብ።
   - **2.2** ከላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች ሞልተህ ከጨረስክ በኋላ የፖስታ ቤቱ ሠራተኛ ዝርዝሮቹን በማመልከቻው ቅጽ ላይ ያትማል።

**ቅጹ ሊለያዩ የሚችሉ ሁለት ክፍሎችን ይይዛል፡**

**የቅጹ የላይኛው ክፍል** በአንተ እጅ የሚቀር ሲሆን ስጦታውን ለመቀበል ማመልከቻ እንዳቀረብክ ማረጋገጫ ነው። ቅጹ የማመልከቻ ቁጥር፣ ማመልከቻው የቀረበበትን ቀን፣ ማመልከቻው የቀረበው ለየትኛው የቀረጥ ዓመት እንደሆነ እንደዚሁም ከማመልከቻው ውስጥ የተወሰኑ መረጃዎች ይይዛል። እንደዚሁም የግብር አገልግሎት ባለሥልጣን ቴሌፎናዊ መረጃ ማዕከል ስልክ ቁጥርና ድረ-ገጽ ይይዛል።

*** በመረጃው ማዕከልና "መኩቫኒም" በሆኑ አገልግሎቶች መረጃዎችን ለመቀበል እንደዚሁም በኢንቴርኔት አማካይነት መረጃ ለመቀበል ያስችል ዘንድ የማመልከቻውን ቅጽ ጠብቆ ማቆየት ያስፈልጋል። የማዕከሉ ስልክ ቁጥር *4954 ("ኮኻቪት ሚሲም")፣ 1-222-4954 ወይም 02-5656400 ነው።**

ስላቀረብከው ማመልከቻ ዝርዝሮችን ከቴሌፎናዊ የስልክ ማዕከል ለመቀበል ብትፈልግ በቅጹ ላይ የታተመው የማመልከቻ ቁጥር ማንነትህን ለመለየት ስለሚያገለግል አስፈላጊ ነው።

**ታችኛው ክፍል** ከፖስታ ሠራተኛው ዘንድ የሚቀር ሲሆን እንደማረጋገጫ ቅጽ ያገለግላል። ይህ ቅጽ ስጦታውን ለመቀበል የሚረዱ ሁሉንም የማመልከቻውንና የአመልካቹን ዝርዝሮች ይይዛል። ዝርዝሮቹ ትክክለኛ መሆናቸውን በተመለከተና ስጦታውን ለመቀበል አመልካቹ መስፈርቶቹን ማሟላቱን ለማሳየት የፖስታ ቤቱ ሠራተኛው በዚህኛው ክፍል ላይ አመልካቹ እንዲፈርም ያደርጋል።

3. በስጦታ ባለመብትነትህ ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ሐሰተኛ መረጃዎችን ባቀረብከው ማመልከቻ ውስጥ ከጨመርክ፣ ወንጀል በመሆኑ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እስራት ሊያስቀጣ ይችላል። በተጨማሪም ስጦታውን ለመቀበል ላመለከትክበት ዓመትና እንደዚሁም ለሁለት ተጨማሪ ዓመቶች ስጦታ የመቀበል መብት አይኖርህም።

## የስጦታ ባለመብትነት እንዴት ይመረመራል? የስጦታው መጠንስ እንዴት ይወሰናል?

1. ማመልከቻው "መኩቫን" በሆነ መንገድ ወይም በፖስታ ቤት አማካይነት ለመሥሪያ ቤቱ ከቀረበ በኋላ የግብርና ባለሥልጣን መስፈርቶቹን ታሟላ እንደሆነ "ኮምፒዩተራይዝድ" በሆነ መንገድ ይመረምራል። እነዚህም የቤተሰብህና ያንተ ሁኔታ (ዕድሜ + የልጆች ቁጥር)፣ በቤተሰብህ ሥር የሚገኙ ንብረቶች፣ ወዘተ. የባለመብትነት መስፈርቶቹን የምታሟላ ከሆነ፣ የሚደርስህ የስጦታ ገንዘብ መጠን ይሰላል።
2. ምርመራው የሚደረገው አመልካቹ የሰጣቸውን መረጃዎች ከሌሎች መረጃዎች ጋር በማጣመር ነው። ሌሎች መረጃዎች የሚባለው ከአሠሪዎች፣ ከ"ቢቱዋሕ ሌኡሚ"፣ ለ"ማስ ሀክናሳ" የቀረበውን ዓመታዊ ሪፖርት (አስፈላጊ በሆኑ ሁኔታዎች ብቻ) የሚያጠቃልል ነው። **አስተውል፡** ተቀጣሪ ሠራተኛ ከሆንክና አሠሪህ ቅጽ 126ን ካላቀረበ፣ ማመልከቻህ እንዳይጓተት በማለት የቀሩትን ዝርዝሮች እንድታሟላ ትጠየቃለህ (ለምሳሌ፡ ቅጽ 106ን ማቅረብ)።
3. የግብር ባለሥልጣን ማመልከቻው ከቀረበበት 90 ቀን ድረስ ወይም እስከ ሐምሌ 15 ቀን 2016 ዓ.ም. ለስጦታው ባለመብት መሆንህንና የስጦታውን ገንዘብ መጠን ይወስናል። ማመልከቻውን ያቀረብክበት ቀን ተብሎ የሚታሰበው ማመልከቻውን **ሙሉ በሙሉ** ካቀረብክ በኋላ ሲሆን አስፈላጊ ሲሆን ተጨማሪ ሰነዶች ማቅረብን ያጠቃልላል። ለምሳሌ፡ በአንቀጽ 2 ለተጠቀሰው ምሳሌ።
4. የግብር ባለሥልጣን በራሱ አነሣሽነት ሆነ አንተ በምታቀርበው ጥያቄ መሠረት የስጦታ መጠኑን በሦስት ዓመት ውስጥ ማስተካከል ይችላል። ይህም የሚሆነው አዲስ መረጃዎች ከተገኙ ወይም የስጦታው መጠን ሲወሰን ስሕተት ተፈጽሞ ከሆነ ነው።

## የምትቀበለው ስጦታ መጠን ምን ያህል ይሆናል?

1. የሚደርስህ የስጦታ ገንዘብ መጠን የሚወሰነው **ከሥራ/ንግድ/ ወይም ሙያህ ከምታገኘው ገቢ፣ ከተጨማሪ ገቢዎችህ** (ከደመወዝ ያልሆነ)፣ እንደዚሁም **የትዳር ጓደኛህ** ከሥራ፣ ከንግድ ወይም ከእጅ ሙያና **ከምታገኘው ገቢና** ሌሎች ተጨማሪ ገቢዎች ነው። እንደዚሁም **በልጆችህ ቁጥርና ባንተ ዕድሜም** ይወሰናል።
2. መጠኑ ከፍ ያለ የ150% ስጦታ ከሚከተሉት ውስጥ ለአንዱ ይሰጣል፡
   (1) አንድ ወይም ከዚያ የበለጡ ልጆች ላሏት ሠራተኛ/በግሉ ለሚሠራ
   (2) አንድ ወይም ከዚያ የበለጡ ልጆች እሱ ዘንድ የሚገኙ ከሆነና ብቻውን ለሚያሳድግ ሠራተኛ/የግል ሠራተኛ

3. ምሳሌዎች*፡

| አማካይ የወር አማካይ የወር ገቢ መጠን (₪) | በወር የሚደርስህ የስጦታ ገንዘብ መጠን<br>ልጆችን ለብቻ የምታሳድግ/ የሚያሳድግ እና አንድ ወይም ሁለት ልጆች ካሏቸው | አንድ ወይም ሁለት ልጆች ያሉት ወንድ/55 ዓመት ገቢ የሞላቸው ልጅ የሌላቸው ወንድ ወይም ሴት |
|---|---|---|
| 0-2,059 | 0 | 0 |
| 2,060 | 120 | 80 |
| 2,500 | 226 | 151 |
| 3,000 | 347 | 231 |
| 3,590-4,790 | 495 | 330 |
| 5,000 | 423 | 282 |
| 5,500 | 250 | 167 |
| 6,141 | 30 | 20 |
| 6,142 እና ከዚያ በላይ | 0 | 0 |

| አማካይ የወር አማካይ የወር ገቢ መጠን የሌላቸው (₪) | በወር የሚደርስህ የስጦታ ገንዘብ መጠን<br>ልጆችን ለብቻ የምታሳድግ/ የሚያሳድግ እና ቢያንስ ሦስት ልጆች ያሏቸው | ቢያንስ ሦስት ልጆች ያሉት ወንድ |
|---|---|---|
| 0-2,059 | 0 | 0 |
| 2,060 | 180 | 120 |
| 2,500 | 335 | 223 |
| 3,000 | 511 | 341 |
| 3,590-4,790 | 720 | 480 |
| 5,000 | 646 | 431 |
| 5,500 | 470 | 313 |
| 6,750 | 30 | 20 |
| 6,751 እና ከዚያ በላይ | 0 | 0 |

*** በስጦታ መልክ የሚከፈለው ገንዘብ መጠን በ1.6.2015 በወጣውና በ1.6.2016 በሚስተካከለው የተጠቃሚዎች የዋጋ አመልካች ("ማዳድ") ላይ የተመረኰዘ ነው።**

*** ከላይ በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረበው ዳታ ("ነቱኒም") አካለ ስንኩል ሠራተኞችን አይመለከትም።**

ከላይ የተዘረዘሩት የስጦታ ክፍያዎች መጠን የሚመለከቱት ከሥራ/ከንግድ ወይም ከእጅ ሙያ ገቢ የሚያገኙትንና ሌሎች ተጨማሪ ገቢዎች የሌሏቸውን ብቻ ነው።

የስጦታው ክፍያ አጠቃላይ የባልና ሚስት ገቢዎችን ከግምት የሚያስገባ በመሆኑ ማመልከቻውን የሚያቀርበው ግለሰብ "ተጨማሪ ገቢ" ወይም የትዳር አጋር ከሥራ/ከንግድ ወይም ከእጅ ሙያ ገቢ የሚያገኙት ገቢና ሌሎች ተጨማሪ ገቢዎች የሚከፈለውን የስጦታ ገንዘብ መጠን ለማሳነስ ወይም ለማሰረዝ (ከታች ቀጥሎ እንደሚዘረዘረው) ይችላል።

4. ሊደርስህ ከሚገባህ የስጦታ ክፍያ መጠን **ያነሰ** ተከፍሎህ ከሆነ፣ የጐደለው ገንዘብ የ"ማዳድ"ና ወለድ ልዩነቶች ተጨምረውበት ይከፈልሃል። ሊደርስህ ከሚገባህ የስጦታ ክፍያ መጠን **የበለጠ** ተከፍሎህ ከሆነ፣ ጭማሪውን ገንዘብ እንድትመልስ ትጠየቃለህ። የምትመልሰውም ጥያቄው በቀረበልህ 90 ቀናት ውስጥ ሲሆን የ"ማዳድ" ልዩነቱን ጨምረህ ነው የምትከፍለው።

## የስጦታ ስጦታው መጠን የሚቀነሰው በምን ዓይነት ሁኔታዎች ነው?

1. ያለህ **"ተጨማሪ ገቢ"** (የሥራ ገቢን አይጨምርም) እና **የትዳር ጓደኛህ ገቢ** በምትቀበለው የስጦታ ገንዘብ መጠን ላይ ተጽእኖ አለው። ላንተ "ተጨማሪ ገቢ" ካለህ ወይም ለትዳር ጓደኛህ ከደመወዝ፣ ንግድ ወይም የእጅ ሙያ ገቢና እንደዚሁም ሌላ "ተጨማሪ ገቢ" ካላት የስጦታው ገንዘብ መጠን ከላይ በተዘረዘሩት ገቢዎች መጠን ይቀንሳል።
2. **"ተጨማሪ ገቢ"፡** ከሚከተሉት ገቢዎች ውስጥ አንዱ እንደ "ተጨማሪ ገቢ" ተደርጐ ይታሰባል።

* በማስ ህክናሳ መመሪያ (5)2 መሠረት ገቢ ተደርጐ የሚቆጠር "ቂጽባ" (ለምሳሌ፡ ጡረታ)። ነገር ግን ለአንድ ሠራተኛ በአካለ ስንኩልነት፣ የመሥራት ችሎታ በማጣት ወይም በትዳር ጓደኛ ሞት ምክንያት የሚከፈለውን "ቂጽባ" አይጨምርም።
* በሥራ ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው ወይም በአደጋ ምክንያት ጉዳት ላጋጠማቸው የቢቱዋሕ ሌኡሚ ድርጅት የሚከፍላቸው ክፍያ።

## ስጦታውን እንዴት መቀበል ይቻላል?

1. ***"ሠራተኛ"*** (ተቀጣሪ) - ***ማመልከቻው*** እስከ ***መጋቢት 31 ቀን 2016*** የቀረበ ከሆነ የስጦታው ገንዘብ **በአራት እኩል ክፍያዎች** በሚከተሉት ጊዜያት ይከፋፈላል፡ ሐምሌ 15, 2016፣ ጥቅምት 15, 2016፣ ጥር 15, 2017 እና ሚያዚያ 15, 2017።
   **ማመልከቻው** እስከ **ሰኔ 30, 2016 የቀረበ** ከሆነ የስጦታው ገንዘብ **በሦስት እኩል ክፍያዎች** በሚከተሉት ጊዜያት ይከፋፈላል፡- ጥቅምት 15, 2016፣ ጥር 15, 2017 እና ሚያዚያ 15, 2017።
   **ማመልከቻው** እስከ **መስከረም 30 2016 የቀረበ** ከሆነ የስጦታው ገንዘብ **በሁለት እኩል ክፍያዎች** በሚከተሉት ጊዜያት ይከፋፈላል፡- ጥር 15, 2017 እና ሚያዚያ 15, 2017።
2. ***"ለግሉ የሚሠራ ሠራተኛ"*** - በሥራ ስጦታ ክፍያ ሕግ ላይ በተደረገው ማሻሻያ ቁጥር 8 መሠረት የግል ሠራተኛ ከሆንክና ከንግድና የእጅ ሙያ ባገኘኸው ገቢ መሠረት በ2012፣ በ2013፣ በ2014 እና በ2015 የሥራ ስጦታ ለመቀበል ባለመብት ከሆንክና ያልተጠቀምክበት የስጦታ ክፍያ ካለህ ነው። ትርፉ የስጦታ ክፍያ ጥር 1 ቀን 2017 ዓ.ም. የሚከፈልህ ሲሆን ትርፉ ገንዘብ ላይ 25% ቀረጥ አይከፈልም።

## በስጦታው ባለመብትነት ውሳኔ ላይ እንዴት ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል?

1. የባለመብትነት ውሳኔን በተመለከተ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለህ። የምታቀርበው ይግባኝ **በምክንያት ላይ የተመረኰዘና በጽሑፍ** መሆን አለበት። ይግባኙን የምታቀርበው ውሳኔ በተሰጠህ 30 ቀናት ውስጥ በምትኖርበት ቦታ ለሚገኝ የተመን ቢሮ ሠራተኛ ነው።
2. ያቀረብከውን **ይግባኝ** በሚመለከት የተሰጠህን ውሳኔ የማትስማማበት ከሆነ በመኖሪያህ ቦታ ለሚገኝ የወረዳ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለህ።

## ተጨማሪ መረጃ ከየት መቀበል ይቻላል?

**ተጨማሪ መረጃ** TAXES.GOV.IL ከተሰኘው የግብር ባለሥልጣን ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል። **በድረ ገጹ** ላይ ***የሥራ ስጦታን በተመለከተ አጠቃላይ መረጃ***፣ የስጦታው ገንዘብ መጠን የሚሰላበት መንገድ (ምሳሌዎችን ጨምሮ)፣ **ብዙ ሰዎች የሚጠይቋቸው ጥያቄዎችና መልሶቻቸው እንደዚሁም ጥቂት በኢንቴርኔት አማካይነት የሚተገበሩና ከታች የተዘረዘሩት ነገሮች፡**

- ***የሥራ ስጦታ ክፍያን ለመቀበል ማመልከቻን "መኩቫን" በሆነ መልኩ ማቅረብ***
- ***የሥራ ስጦታ ክፍያን ለመቀበል ባለመብትነትን ማጣራት***
- **በፖስታ ቤት የቀረበው ማመልከቻ ያለበትን ሁኔታ ማጣራት**
- **ባለመብትነትን ለማጣራትና የስጦታውን መጠን ለማስላት የሚረዳ "ሲሙሌተር"**

እዚህ ላይ የቀረቡት ማብራሪያዎች አጠቃላይ ሐሳቦች ስለሆኑ ሕጋዊ ረቂቅ እንደሆኑ አድርጐ ማየት አያስፈልግም። በተጨማሪም በተባዕታይ ጾታ የተጻፈው አንስታይ ጾታንም ይጨምራል።

רשות המסים בישראל

ማዕከላዊ የስልክ መሥመር፡ *4954 1-222-4954

*מסים

www.taxes.gov.il | 02-5656400

- እዚህ ላይ የቀረቡት ማብራሪያዎች አጠቃላይ ሐሳቦች ስለሆኑ ሕጋዊ ረቂቅ እንደሆኑ አድርጎ ማየት አያስፈልግም። በተጨማሪም በተባዕታይ ጾታ የተጻፈው አንስታይ ጾታንም ይጨምራል።

የደንበኞች አገልግሎትና ገለጻ ክፍል፣ የእስራኤል የግብር ባለሥልጣን/ መጋቢት 2016 מסל